# የጥላቻ ፖለቲካን እንተዉ አገራችንን እንዴት እንለዉጥ ብለን እናስብ!

ባህል ሁኖብን ስለምናውቃቸው ሰዎች መግለጽ ስንፈልግ ሰዎች ጋ ካለን ቀረቤታ ጋር አዛምደን መሆኑ የሰዎችን መልካም ስራቸውን ያለቅጥ አጋነን በማሞገስና የሰዎችን እኩይ ተግባር ደግሞ ያለ ምህረት ስብእናቸውን ጭምር አዋርደን በመተቸት  የሰወችን የስራ ክንዋኔ በሚዛኑ ፍርድ የመስጠት ልምድ ገና ያልዳበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሄን እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር አንዱን የግሉን የህዝብ ሌላዉ የህዝቡን የግሉ ጠንካራዉን ደካማ ደካማዉን ጠንካራ ዉሸትን እዉነት በሌላ በኩል አዉነትን ዉሸት ያደርጋሉ የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች ህዝብን በተሳሳተ መንገድ ለማሰለፍ ስልት በመያዝ ከጭፍን ጥላቻ በመነሣት ህዝብ የሚጠቅመውንና የሚበጀውን ለይቶ እንዳይመዝን እድል ለመንፈግ ይሰራሉ፡፡ ህዝብን ማደናገር ያልነበሩና የማይታሰቡ አሁን በአስደማሚ ሁኔታ እየተከናወኑ ያሉ መልካም ተግባሮች ህዝቡ የሚያዉቀዉንና የሚያየዉን ሳይቀር አልተሰራም የለም ብለዉ በድፍረት ሲጽፉ ሲናገሩ እጅግ ያስገርመኛል፡፡ ነገር ግን  ዛሬ ያለዉን ለዉጥ እድገት በአገራችን አይተነዉ የማናዉቀዉ ቢሆንም የተለያዩ ጉድለቶች የሉም ለማለት አይደለም የተጠቃሚዎች ፍላጎት ከአገራችን መንግስት አቅምና ተነሳሽነት የበለጠ እየቀደመ መሆኑንም እገነዘባለሁ፡፡ ነገር ግን ተቋዋሚ ሲባል የተሻለና ለህዝብ ጉድፍን የሚያሳይ ነበር እንጅ ጥፋት ተኮር ዘመቻ ላይ ማተኮራቸው ለህዝብ ነው ለፖለቲካ ስልጣን ጥም የቆሙ ብየ ስመዝን ህዝባዊነታቸው እጅግ ተጓድሎ ጎልቶ ይታያል፡፡

እኔ ጋዜጠኛ ሁኘም  አይደለም፡፡ የመፃፍ ችሎታም የለኝም፡፡ ዕሁፉም ላይ በጽሁፉ ቅርጽና ውበት እንዲሁም በጽሁፉ ይዘት ብስለት ላይ አንባቢያን ብዙ ትችት እንደሚኖራችሁ እገምታለሁ፡፡ እንደ ኢትዩጵያዊነቴ በሀገራችን ጉዳይ ላይ ለሀገሩ ሌት ከቀን እንደሚታትሩት እኔም አልደራደርም፡፡ ከዚህ በላይ ስለ ራሴ ብዙ ለማለት

አልደፍርም፡፡ እንደማንኛውም ሰው በተሰማኝና በአሣሰበኝ ጉዳይ ላይ ሀሣብ ለመሰንዘር ነው፡፡ በዚህም አስተያየቴን ያነበቡት ሁሉ እንደሚጋሩት ተስፋ አደረጋለሁ፡፡

ከወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሣት ጋር ተያይዞ የነቀፌታ ፖለቲካ አራማጆች ጉዞ በተረዳሁት መጠን ስመዝነው የዉይይታችን ደረጃ እየወጣብን ስለመጣ ትኩረት እንድሰጥ አድርጐኛል፡፡ እንደምናውቀው "በምርጫው የተወለደ የለም" ይባላል፡ እኛም እንደ እድል ሁኖ ሁከት ብጥብጥ እና ትርምስ መናገሻ ሁና በቆየችው አገራችን ኋላቀርነት ያለቅጥ በተንሠራፋባት አፍሪካ ውስጥ መፈጠራችንን አላማረርንም ድህነትንና ኋላቀርነትንም በፀጋ አልተቀበልነውም፡፡ ለዚያም ነው የሰው ልጅ ከችግሮቹ ለመላቀቅ አነሰም በዛም መፍጨርጨሩ ተፈጥሮአዊ ባህሪው መሆኑን በተግባርም የሰውልጅ የደረሰበት የስልጠኔ ደረጃ ማስረጃ ነው፡፡ በአገራችንም ህዝባችን ቀደምት የስልጣኔ አሻራ ያለው ቢሆንም ሠርቶ የመለወጥ ባህሪዉን አደራጅቶ የልማት ስራ ላይ ማስቀጠል ባለመቻሉ ለረጅም ጊዜ በድህነትና ኋላቀርነት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ መቆየታችን ግልፅ ነዉ፡፡

ከላይ የተነሳሁበት መንደርደሪያ ወደ ታሪክ ለመመለስ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከቅርቡ አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ ያግዘን ዘንድ በመጠኑም ቢሆን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ኢህአዴግ አስከፊውን የደርግ ስርአት ከአስወገደ በኋላ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በአገሪቱ በሰላም በልማትና በዲሞክራሲ ምን ተጨባጭ ለውጥ አመጣ? ብሎ መጠየቅ እንደ ዜጋ ብልህነት ሲሆን ውጤቱንና ለውጡን ለመመዘን አገሪቱ የአፈራረቀቻቸውን ስርዓቶችና ያለፈውን ጊዜ መለስ ብሎ መመልከት ደግሞ አስተዋይነት ነው፡፡ እዚህ ላይ አነፃጽሬ ላቀርብ አይደለም፡፡ ሆኖም እኛን ዜጎችን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ተጠቃሚ መሆን የጀመርንበትን ለይቶ መደገፍ የማይጠቅመዉን መቃወም በጅምላ አለማድረግ ለአገር እድገት ጠቃሚ ነዉ ብየ ስለማስብ ነዉ፡፡ ስለዚህ የጥላቻ ፖለቲካ አራማጅ ሀይሎች ተግባራቸውን ነው አጥበቄ መሞገት የምፈልገው ህዝብን ማስተዳደር በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በተለይ እንደኛ ሀገር በድህነትና በኋላቀርነት ተተብትቦ የቆየ አገር መምራት ይቅርና በበለፀጉት አገሮች እንኳ ያለውን ፈተና የምናየው ነው፡፡ ነገር ግን ህዝብን/ሀገርን/ እንመራለን በሚል ሽፋን ተፈልፍለው የተኮለኮሉ የጥፋት

ተኮር አስተሳሰቦችና ተግባሮች እኛን አብዛኛዉን ንጹህ ዜጋ የሚጎዳ መሆኑን አጥብቀን ልንረዳዉ ይገባል ስል፤

## ህዝባዊነትን በጥላቻ ፖለቲካ አራመጆች

- በአንድ ሀገር ህዝብን ለመምራት አገርን ለማስተዳደር የፖለቲካ ፖርቲዎች ሲመሠረቱ ህዝባዊ መሠት ኑሮአቸው ለህዝብ ጥቅም ያስገዙ መሆን አለባቸዉ፡፡ በዚህም ለሀገር ይጠቅማሉ ይበጃል ብለው ያመኑበትን የፖለቲካ ፍልስፍና ርዕዩት በዝርዝር ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፈው ልዩነታቸውን ለህዝብ በማቅረብ ለፍትሀዊ ውድድር እራስን ማዘጋጀት ሲችሉ ነው፡፡
- እኛ ጋ ያለ በዚህ ደረጃ ዝግጅት ስለሚጎላቸው ለመዘጋጀትም በቂ አቅም ወይም እውቀት ስለሌላቸው፤ ከዚህም ተነስተው ፍትሀዊ ውድድር የማያዋጣቸው በመሆኑ በጭፍን ጥላቻ በጅምላ ይወቅሣሉ፣ያወግዛሉ፣ይዘልፋሉ፣ እና የጥላቻ ፖለቲካ ይከትባሉ፡፡
- ህዝብ የሠራውን እጅግ ግዙፍ የልማት ሥራዎች ሣይቀር በጠራራ ፀሐይ ይክዳሉ፣ ያንኳስሳሉ፡፡ ምንም ቢሆን አገራችን አሁን ለደረሰችበት አበረታች እድገት ኢህአዴግ  የመሪነት ሚና ነው እንጂ ሚኖረው ህዝቡን ሊተካ አይችልም በህዝብ የተገነቡ ልማቶችን ይንቃሉ፣ህዝብን እንደ ህዝብ ዝቅ ያደርጋሉ፡፡
- እኔ የሚያሣዝነኝ እንደ ሀገር ብድርና እርዳታ  አገሪቱ እንዳታገኝ አጋሮችን ይሞግታሉ ይከለክላሉ፣ ለማን ሀገር ነው የተደራጁት ለየትኛው ህዝብ ነው የሚሠሩት ሌላ ሀገር አላቸው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሣታችን አይቀርም፡፡ በእርገጥ ይደራጃሉ ይመሠረታው ሞቅ ሞቅ ያደርጉና መንበረ ስልጣን ላይ ለመዉጣት ይቸኩላሉ ይንገበገባሉ ረጅም ጊዜ ሣይቆዩ በውስጣቸዉ በተፈጠረ ሽኩቻ ይበታተናሉ መልሰውም አንደኛዉ አንደኛውን ይኮንናሉ ፡፡ ይህ ከምን የመነጨ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የትችት ናዳ የሚያወረዱበት ኢህአዴግ እኮ በሃሳብ ልዩነት የፖለቲካ ፓረቲ ማቆቋም ፈፅሞ በማይቻልበት ተናጥላዊ ሃሳብ መተንፈስ

በማይታሰብበት በአስከፊዉ ጊዜ በፅናት ታግሎ አስከፊዉን የደርግ ስርአት ጠራርጎ በማስወገድ የአዲስቷን ኢትዮጵያ  የህዳሴ ጉዞን በማብሰር አሁን አስተማማኝ ሰላም እየጎመራ ላለዉ የልማት ዲሞክራሲ ቱርፋቶች በጽናት ተጉዞ እዚህ ደረጃ አድረሶናል፡፡ ለህዝብና ለሀገር የቆመ ህዝብን ለመምራት ራሱን ያዘጋጀ እንዴት ፅናትና እምነት ይጐድለዋል? መልሱን ለአንባቢያን ትቻለሁ፡፡

–

## ሀላፊነት የጐደለው አካሄድ ይከተላሉ ፡-

አገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና የቱባ ባህል ባለቤት ነች፡፡ ያለፈው ታሪካችን ብዙ ተብሎለታል ጫናዎችና ረገጣዎች  ቢኖሩም ተቋቁሞና ተቻችሎ ረጅም ዘመናትን አብሮ አሣልፏል፡፡ አሁን ያሣለፈውን ግፍና ስቃይ ሚሸከምበት ትክሻ የለውም ጊዜውም ይህን አይፈቅድም፡፡ አሁን ለተፈጠረው አስተማማኝ ሰላምና  የመከባበር፣ የመፈቃቀድ፣ የአብሮነት አንድነት ሁሉም ብሔሮች ምስክርነት የሰጡበት ጉዳይ ነው፡፡ ሁኖም ከቆየው ታሪክ በመነሣት አንድ ቢሉ ይደግፋሉ መልሰው ይኮንናሉ ተረገጥህ ተነስ በማለት ይቀሰቅሣሉ ተዋረድክ ብለው አታሞ ያጮሀሉ አንዱ በአንዱ እንዲነሣ ጥላቻ እንዲዳብር ይቀሰቅሣሉ ሁከትና ትርምስ እንፈጠር ሰላም እንዲደፈርስ አገር እንዲበታተን ጠንክረው ያለእረፍት ሀላፊነት የጎደለው ተግባር ይፈጽማሉ፡፡ እዚህ ላይ አንድ አብነት ማንሳት ተገቢ ነዉ፡፡

በቅረብ በብአዴን አንድ ከፍተኛ አመራር ተነገረ የተባለዉና በቆርጦ ቀጥል የኮንፒዉተር ዘዴ እንደተቀነባበረ የተረጋገጠዉ የጥፋት ዘመቻ ቴክኖሎጅ ለጥሩ ነገር ሳይሆን ለጥፋት የሚጠቀሙ ኃይሎች መጥፎ ተግባር ነዉ፡፡የቴክኖሎጅዉን እድገት የማደንቅ ብሆንም ይህን ቴክኖሎጅ በመጠቀም የሚሰሩ የሸፍጥ ስራዎችን በዚህም ህዝብን የማደናገር ድርጊቶችን ይህን ተከትሎም ሌት ከቀን ህዝብን ለመለወጥ የተዋደቁ ያሉ አመራሮችን ስም የማጉደፍ አካሄድ አጥብቄ እቃወማለሁ፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁ ምስሎችንና ድምጾችን ከታማኝ የመረጃ ምንጮች ካለሆነ ማመን እንዴት ይቻላል፡፡ ሊታመንም አይችልም፡፡ በቅረቡ አንድ ምስል ተመለከትሁ የአህያን ስነ አፈጣጠር ተላብሶ የተፈጠር

የሰዉ ልጅ ከቶም ሊኖር አይችልም፡፡ በተመሳሳይ እንደ አህያ የሚያስብ የሰዉ ልጅ ሊኖር አይችልም፡፡ ምስሉ ላይ የተመለከትሁት ቆርጦ በመቀጠል የኮምፒዉተር ጥበብ ተቀነባብሮ ድንቅ የሆነዉን የሰዉ ልጅ ተፈጥሮና የአስተሳሰብ ልግስና በእጅጉ የሚያዋርድ ተግባር ነዉ፡፡ ታዲያ በአይናችን እያየነዉ ያለዉን ምስል እንዴት እንመን? ይህን የመሰለ ኃላፊነት የጎደለዉ ቅንብር እየተመለከትን የማመዛዘን ችሎታ ያለን ብልሆቹ የሰዉ ልጆች በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁትን ሁሉ እዉነት ነዉ ብለን እንዴት ልንቀበል እንችላለን፡፡ ፈጽሞ አንቀበለዉም፡፡

ከላይ የጠቀስኩትን የመሰለ ቅጥ ያጣ ጥፋት ተኮር እንቅስቃሴ ዉጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ግልጽና የዜሮ ድምር ፖለቲካ አካሂድና በእኔ እምነት ባዶነትና ሃላፊነት የጎደለዉ ተግባርና ቆምሁልህ የሚሉትን ህዝብ የበደሉ በመሆኑ እንደ ዜጋ ጉዳዩ አሳስቦን በቃችሁ ልንላችዉ ይገባል፡፡ እያልሁ እነዚህ አጥፍቶ ጠፊዎች ቆርጦ ቀጥሎች ከዚህ የክፋት ተግባራቸዉ እስካላቆሙ ድረስ የህዝብን ጥቅም ወግኘ መፋለሜ ይቀጥላል፡፡

**ቸር ይግጠመን!**

**<u>ከእዉነቱ መጣልህ!</u>**

ewuntumtaleh@gmail.com